17
33 36

# ዜና ቤተ ክርስቲያን



ለጵጵስና የተመረጡት ፭ቱ ቆሞሳት ።

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ፲፱፻፳፩ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianortodox.org

[illegible handwriting]

| ማ ው ጫ ። | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ (በጸጋ ላይ ጸጋ) | ፪ |
| ፪ | የ፯ ቀሞሳት የጵጵስና ምርጫ አፈጻጸም | ፭ |
| ፫ | ለጵጵስና የተመረጡት ፯ቱ ቀሞሳትና የሕይወት ታሪካቸው በጭሩ ። | ከ፰ |

[illegible handwriting]

www.ethiopianortodox.org

በመንፈሳዊው ሕይወት ሕዝቡን ለማገልገል በየጊዜው የሚመረጡቅ ብፁዓን ጳጳሳቅ ከባድ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን መገንዘብ ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊውን ትውልድ ወደ መንፈሳዊው ሕይወት ለመምራት የተመረጡትን እግዚአብሔር መንፈሳዊ ኃይል እንዲሰጣቸው እንመኝላቸዋለን ።

---

# የ፫ቱ ቆሞሳት የጵጵስና ምርጫ አፈጻጸም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሕግና ሥርዓት መሠረት፣ ከመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ. ቤት በወጣው ትእዛዝና ደንብ በተቋቋመው ልዩ ኮሚቴ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓም ስድስት ቆሞሳት ለጵጵስና በድምፅ ብልጫ ተመርጠዋል ።



ለጵጵስና የተመረጡት ፫ቱ ቆሞሳት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ቀርበው ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ

እነዚህ ሕሩያን ቆሞሳት የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አቅራቢነት በኢዩቤልዩ ቤተ መንግሥት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ቀርበው ለጵጵስና ስለመመረጣቸው ሥርዓተ መሐላ ፈጽመዋል በሥርዓተ መሐላውም አፈጻጸም ጊዜ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ልዑልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ፣ ልዕልት የሻሸወርቅ ይልማ፣ልዑል ልቅ ግራ ግዛው፣ ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን የሐረር መስፍን



www.ethiopianortodox.org

የእንግሊዝኛና የዐረብኛ ቋንቋ
ያውቃሉ መምህር ተስፋ
ማርያም ወልደ ሥላሴ ለኢትዮ
ጵያ እርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ
ክርስቲያን የረዥም ጊዜ የተቀ
ደሰ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ከብዙው በጥቂቱ በጠ/ ቤተ
ክህነት ጽ| ቤት የሊቃውንት ጉ
ባዔ ሰብሳቢ ሆነው ሠርተዋል ፡፡
እንዲሁም የአዲስ አበባ ደብረ
ጽጌ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን
አስተዳዳሪ ሆነው በመሾም በአ
ስተዳደር አዋቂነታቸው ከመመ
ስገንና ከመወደድ ጋር አስተዳ
ድረዋል ። መምህርተስፋማርያም
ወልደሥላሴ አሁን የሚሠሩት
በጅማ ሀገረ ስብከት የሊቀ ጳጳሱ
እንደራሴ ሆነው ነው ። በተጠ
ቀሰው ሀገረ ስብከት በእንደራሴ
ነት ለሰባት ዓመት ያህል በትጋት
አገልግለዋል መምህር ተስፋ ማ
ርያም ወ/ ሥላሴ በጅማ ሀገረ ስብ
ከት በሐዋርያነት ከተላኩበት
ጊዜ ጀምሮ የስብከተ ወንጌል
ድርጅት በማቋቋም በጊዜ ብዛት
የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት
በማሳደስ የሀገረ ስብከቱን ጽ፤
ቤት በአስፈላጊው ጉዳይ በማ
ሻሻል ሐዋርያዊ ግዳጃቸውን
ፈጽመዋል ። መምህር ተስፋ
ማርያም ወልደ ሥላሴ ዘወትር
በሚያሳዩት የተቀደሰ ርምጃ በ
ጅማ ሀገረ ስብከት በገዥዎችም
ሆነ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተ
ወዳጅነት አላቸው ። መምህር
ተስፋ ማርያም ወልደ ሥላሴ
የስብከት ችሎታ ያላቸው፤ በን
ጽሕና በድንግልና የተመሰገኑ ፤
አስተዳደር አዋቂ ፤ ትሁትና ግ
ብረ ገብ ፤ ለጾምና ለጸሎት የተ
ጠመዱ ሁሉን እኩል የሚወዱ
ፍቅረ ቢጽና ፍቅረ እግዚአብሔ
ር ያላቸው ግሑስ አባት ናቸው ።



www.ethiopianortodox.org